Ministry of Revenues
የገቢዎች ሚኒስቴር

ገቢያችን ህልውናችን

15ኛ ዓመት | ቁጥር 170 | የካቲት 2016 ዓ.ም | በነፃ የሚታደል

በውስጥ ገፆቻችን

«የዓለም አቀፉ የጉምሩክ ድርጅት አባል በመሆናችን ብዙ ጥቅም አግኝተናል»
ገጽ 3

አሳሳቢው የልጆች ከልክ ያለፈ ውፍረት
ገጽ 5

ገቢዎችን የተመለከቱ ወቅታዊ፣ ትኩስ እና የተሟሉ መረጃዎችን ለማግኘት፡- በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎቻችን ይጎብኙ

1. በድረ ገጽ፡- www.mor.gov.e
2. በቴሌግራም፡- https://t.me/MoREthiopiaOfficial/169
3. በፌስቡክ፡- https://www.facebook.com/ERCA.info or ministryofrevenuesofethiopia /የገቢዎች ሚኒስቴር/
4. በዩትዩብ፡- https://www.youtube.com/@ministryofrevenuesofethiop1677/videos Or ministryofrevenuesofethiopia
5. በቲክቶክ አጫጭር መረጃ https://vm.tiktok.com/ZM61hdty2/

በቴሌቪዥን ፕሮግራሞቻችን

6. ዋልታ ቴሌቪዥን ሰኞ ማታ ከ 2፡30 ጀምሮ
7. ፋና ቴሌቪዥን ሐሙስ ማታ ከ2፡00 ዜና በኃላ
8. ኢቲዮጵያ ቴሌቪዥን /ኢ.ቢ.ሲ/ ቅዳሜ ማታ ከ2፡00 ዜና በኋላ

በሬድዮ ፕሮግራሞቻችን

9. ፋና ኤፍ ኤም ሬድዮ 98.1 ሐሙስ ማታ ከ2፡30 ጀምሮ
10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬድዮ 93.1 ማክሰኞ ጠዋት ከ2፡30 ጀምሮ
11. በወርሃዊ ጋዜጣችን፡- ገቢያችን ህልውናችን

«ዳኤ ቡሹ!»

በስኬት የታጀበው የሰባት ወራት ጉዞ

በሺመልስ ሲሳይ

«ዳኤ ቡሹ! ዳኤ ቡሹ! ዳኤ ቡሹ!»፡- ይህ፤ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮች የሰባት ወራት የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ መክፈቻ ላይ በሲዳማ የሀገር ሽማግሌዎች የቀረበ የ«እንኳን ደህና መጣችሁ!» የሲዳማ የሀገር ሽማግሌዎች የምረቃ መክፈቻ እና መዝጊያ የመልካም ምኞት መግለጫ ነው፡፡

ሀዋሣ ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 275 ኪሎ ሜትር የምትርቅ ከተማ ነች፡፡ ከተማዋ የተቆረቆረችው በ1952 ዓ.ም. ሲሆን ስያሜዋ የተወሰደው ከሀዋሳ ሀይቅ ነው፡፡ የሲዳሚኛ ትርጉሙ «ሰፊ» የሚለውን ይይዛል፡፡

ከአዲስ አበባ በ275 ኪሎ ሜትር የምትርቀው ሀዋሳ 157.2 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት አላት፡፡ የክፍለ-ከተሞቿ ብዛት ስምንት ሲሆኑ ቀበሌዎቿ 32 ናቸው፡፡

ከተማዋ የበርካታ ቱሪስቶች መዳረሻ ስትሆን ይህ ይዞታዋ ለበርካታ የመንግሥት እና የግል ድርጅቶች ስብሰባ ማካሄጃነት ተመራጭ አድርጓታል፡፡ የገቢዎች ሚኒስቴር እና የጉምሩክ ኮሚሽን አመራሮችም የ2016 የሰባት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማቸውን ከየካቲት 1 እስከ 4/2016 ዓ.ም አካሂደውባታል፡፡

በግምገማ መድረኩ ላይ የገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሤ እና የጉምሩክ ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ፤ የገቢዎች ሚኒስትር ዴኤታዎች እና ምክትል ኮሚሽነሮች

የገቢዎች ሚኒስትር ወ/ሮ ዓይናለም ንጉሴ እና የጉምሩክ ኮሚሽነር አቶ ደበሌ ቃበታ፤

ተገኝተዋል፡፡ እንዲሁም የሁለቱም መ/ቤቶች የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጆች እና ምክትል ሥራ አስኪያጆች እንዲሁም የዘርፍ ዳይሬክተሮችም ተሳታፊ ነበሩ፡፡ በግምገማው ቀልጣፋ፣ ዘመናዊ እና ተደራሽ የቀረጥና ታክስ አስተዳደር ሥርዓት የማጎልበት ሥራዎች፣ የአሠራር ልህቀት፣ ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም እና የግብር ከፋዮችን የቀረጥና ታክስ ሕግ ተገዢነት ሥራዎች አፈጻጸም ተገምግመው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

የጉምሩክ ኮሚሽን ባለፉት ሰባት ወራት 121 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ 111 ቢሊየን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 91.4 በመቶ አሳክቷል፡፡ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ9.5 በመቶ ብልጫ አለው፡፡ የሞጆ እና የቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች 65 ቢሊዮን ብር የሰበሰቡ ሲሆን የነዚህ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ገቢ ከተሰበሰበው 58.42 በመቶ ይሸፍናል፡፡ ኮሚሽኑ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን ባደረገው የፍትሐ ብሔር ክርክር የመርታት አቅሙን በመዝገብ 83.43 በመቶ እና በገንዘብ 91.9 በመቶ ያደረሰ ሲሆን በአማካይ 87.66 በመቶ አድርሷል፡፡

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

«ሁሉንም ክፍያዎች በባንክ በኩል ብታደርጉልንማ...!»

«ገቢዎች፤ የግብር ክፍያን በባንክ በኩል ማድረጉ ሥራችንን አቅልሎልናል፡፡ በፊት ግብር እና ታክስን ለመክፈል ገቢዎች ሔደን በወረፋ ሰልፍ የምናጠፋው ጊዜ ~~ብዙ ነበር፡፡ ከ~~ምናጠፋው ጊዜ ሌላ እንግልትም ነበረው፡፡ አሁን ክፍያውን በባንክ መፈጸማችን ከነዚህ ችግሮች አላቆናል፡፡

ያኔ ለክፍያ በየወሩ ገቢዎች የምንሔድበት አሠራር በየሦስት ወሩ መሆኑ ጥሩነቱ ባንክም ላይ ስንከፍል በሦስት ወር ተደርጎ መቀጠሉ ነው፡፡ ነገር ግን የከፈልንበትን ደረሰኝ ይዘን ገቢዎች እንድንሔድ መደረጉ የፈራነው ወረፋ ውስጥ ስለወሰደን መረጃውን ከባንክ መውሰድ ቢቻል፡፡

ከዚህ ሌላ የሠራተኛ ደመወዝ ገቢ ግብርን እና የጡረታ ክፍያንም በባንክ በኩል እንድናከናውን ቢደረግ ከላይ ያገኘነውን ጥቅም በዚህም እንድናገኝ ያደርግልናል»

የውብሥራ ዕደ-ጥበብ ድርጅት ባለቤት

ገቢዎች ሚኒስቴር ግብርን በባንኮች እና በቴሌ ብር ለመክፈል እንዲቻል ከሰኔ 2013 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ የካቲት 1/2016 ዓ.ም. ድረስ ከ18 ባንኮች እና ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር ስምምነት ተፈራርሞ ተግባር ላይ አውሏል፡፡ አሠራሩ ለግብር ከፋዮችም፣ ለግብር ሰብሳቢ ተቋማትም

ከግራ ወደ ቀኝ፤ የአማራ ባንክ ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጫንያለው ደምሴ፣ የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወ/ሮ መሠረት መስቀሌ እና የፀሐይ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ አቶ ወሰን ዓለምዬ ስምምነቱን ሲፈራረሙ፤

ብዙ ጥቅም በመስጠቱ ወደሌሎች ባንኮችም አገልግሎቱን አስፍቶ ሰሞኑን ደግሞ ከፀሐይ እና ከአማራ ባንኮች ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሟል፡፡

ስምምነቱን የፈረሙት በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ኦፕሬሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴዔታ ወ/ሮ መሠረት መስቀሌ፣ የአማራ ባንክ ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጫንያለው ደምሴ እና የፀሐይ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ተወካይ አቶ ወሰን ዓለምዬ ናቸው፡፡

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ርዕሰ አንቀጽ

የኛንም መታሰቢያ ለማኖር

ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳንሆን አፍሪካውያን፤ ከአፍሪካም አልፎ የመላው ዓለም ጥቁሮች፤ በተለይም በቅኝ ግዛት ውስጥ የነበሩት ሀገራት የ‹‹አንገዛም›› ባይነት ልምድ ወስደው በብዙ ትግል ራሳቸውን ነጻ ያወጡት በዓድዋ ድል መንፈስ ነው፡፡

የዓድዋ ድል በ1888 ዓ.ም. ዓድዋ ላይ የተገኘው አውሮፓውያን አፍሪካን ለቅኝ ግዛትነት ሲቀራመቱ ሀገራችንን ድርሻቸው ያደረጉትን ጣሊያንን አሳፍሮ ለመመለስ ተምመው በወጡ ኢትዮጵያውያን ነው፡፡ በዚህ ተጋድሎ ከመላዋ ኢትዮጵያ የተውጣጡ ሀገር ወዳድ ዜጎች የተመሙት ከንጉሡም፣ ከርስ በርሳቸውም የነበረውን ልዩነት ለጊዜው ትተው ነበር፡፡

የነዚህ ጀግኖች መታሠቢያ በየዓመቱ ፒያሳ በሚገኘው የዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ የሚከበር ሲሆን ዘንድሮ ደግሞ ለየት የሚለው እዚያው ፒያሳ ላይ ለጀግኖቹ ማስታወሻ ሙዚየም መቆሙ ነው፡፡ ይህ የመታሠቢያ ሙዚየም የካቲት 4/2016 ዓ.ም. መመረቁ ይታወቃል፡፡ ሙዚየሙ ከመገንባቱ አስቀድሞ ለረጅም ዓመታት በግንባታ ስም ታጥሮ የቆየ ሲሆን ከዚያ በፊት ደግሞ ኳስ ሜዳ እና ሥርዓት ያልተበጀለት አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ ቦታው የወጪ ወራጁ መፀዳጃ ጭምር ስለነበር አላፊ አግዳሚውን በሚሰነፍጥ ሽታ ይረብሽ ነበር፡፡

አሁን ግን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቦታውን የኢትዮጵያውያን ጀግንነት እና ኩራት ምንጭ ለሆነው የዓድዋ ድል መታሰቢያ እንዲሆን ወስኖ ገጽታውን የሚለውጥ ሙዚየም አስገንብቶበታል፡፡ የዚህ ሙዚየም ውጪያዊም ሆነ ውስጣዊ ገጽታ ዓድዋን እና የዓድዋን ባለታሪኮች ታሪካዊ ምንነት እና ማንነት የሚያሳይ ነው፡፡ ይህ፤ ትውልዱ ሙዚየሙ ውስጥ ከተቀመጡትም፤ ወደፊት ከሚቀመጡትም የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች ታሪክ ወርሶ ሀገሩን የሚወድ እና የሚጠብቅ እንዲሆን አንዱ አጋዥ ይሆንለታል፡፡

ይህ ገጽታው ለዕይታ የማይስብ የነበረው ሥፍራ ለመዋብም፣ ታሪክን ለመዘከርም የበቃው በዋናነት ግብር ከፋይ በሚከፍለው ግብር ነው፡፡ ግብር ከፋዮች ያለማንም ገፋፊነት ወይም አስገዳጅነት በሚከፍሉት ግብር ትናንት የማይደፈር ተደርጎ ይታሰብ የነበረውን የሕዳሴ ግድብ መገንባት ተጀምሮ ዛሬ ማጠናቀቂያው ምዕራፍ ላይ መደረሱ ይታወቃል፡፡ አሁን ደግሞ በሌሎቹ ፕሮጀክቶች እና በዚህ ሙዚየም የድካም ውጤት ሲታይ ከሚመሰገኑት አጋዦች ዋነኞቹ ግብር ከፋዮች ናቸውና ሊደሰቱ ይገባል፡፡

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የመንግሥት እጅ አጥሮ ያለጥቅም ተቀምጠው የምናያቸው መሬቶች እንዴት ባለመልኩ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለባቸው የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ልምድ መቅሰሚያ ነው፡፡

ቀደም ሲል የተጀመረ ቢሆንም በተለይ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በገቢዎች ሚኒስቴር ዋናው መ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲሁም በክልል እና ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ጽ/ቤት እየተከናወነ ያለው የታማኝ ግብር ከፋዮች ሽልማት የተሸላሚዎች ማንነትን እንደ ዓድዋ ሙዚየም ማስዋብ ነው፡፡ ሙዚየሙ ከዚህ በኋላ የሰዎችን ቀልብ እንደሚስብ ሁሉ ተሸላሚ ግብር ከፋዮችም እንደየደረጃቸው ባገኟቸው ክብሮች በደንበኞቻቸው ተአማኒነትን አትርፈው ከበፊቱ የበለጠ ገበያቸው ይደራል፤ ለመንግሥትም የሚያስገኙት ገቢ እየጨመረ ይሔዳል፡፡

የአድዋ መታሰቢያ ያረፈበት ቦታ ቀደም ሲል ተገቢም፣ ያልተገባም ተግባር ሲፈጸምበት እንደነበር ይታወቃል፡፡ ያ ጊዜ አልፎ ሀገራዊ ብቻ ሳይሆን ዓለማቀፋዊ ይዘታ ባለው መልኩ መገንባቱ ገጽታውን ቀይሮታል፡፡ ግብር ከፋዮቻችንም ትናንት የነበረ ታሪካቸው ከግብር ስወራ፣ ያለደረሰኝ ከመሥራት እና ከሌላ ሕገ-ወጥ ተግባር ጋር የተያያዘ ከነበረ ያን ትቶ ሕጋዊ መሆንን ተግባራዊ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ሕጋዊ መሆን ብቻ ሳይሆን በሕገ-ወጥ አካሔዳቸው ጥቅሟን አጥታ የነበረች ሀገራችንን በቁጭት እና በእልህ መካስ ይገባቸዋል፡፡

ሀገራችን ለትውልድ የሚተላለፉ ብዙ ቅርሶች እና ክዋኔዎች ቢኖሯትም ደረጃቸውን የጠበቁ አድርጎ ለማውረስ የሀገር ሀብት ውስንነት አለ፡፡ ስለዚህ ለዚህ አቅም ኖሯት የዓድዋ መታሰቢያ ዓይነት በርካታ ግዙፍ ፕሮጀክትን እውን እንድታደርግ ሁላችንም የሚፈለግብንን ግብር በፈቃደኝነት በመክፈል የገቢ አቅሟን ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ጀግኖቹ ከዘመቻው በፊት የነበራቸውን ቅሬታም ሆነ ልዩነት በይደር አቆይተው በመዝመት ድል እንዳደረጉት፤ ግብር ከፋዮቻችን የቱንም ያህል በመንግሥት ቅሬታ ቢኖርባቸው እንኳ ልዩነት የማይገድበውን የግብር ግዴታ መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የዓድዋ ድል መታሠቢያ ሙዚያም ታሪክን ለትውልድ ከማውረስ ባሻገር ሀገር የገቢ አቅሟ ከዳበረ የትኛውንም ፕሮጀክት መገንባት እንደምትችል ማስመስከሩ ብቻ ሳይሆን በአጭር ጊዜም ማድረስ እንደሚቻል ያሳየ ነው፡፡ እንዲህ የሆነው አሠሪው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክትትሉን ጠበቅ ስላደረገ ነው፡፡ ይህ ቁርጠኝነት ለንግድ ድርጅቶች ባለቤቶች እና ሥራ አስኪያጆች የሚሰጠው ትምህርት፤ ድርጅቶቻቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ክትትላቸው ሊለይ እንደማይገባ ነው፡፡ ክትትሉ ከዚህ ሌላ፤ አንዳንዴ ከነርሱ እውቅና ውጪ የሚፈጸምን ያለደረሰኝ መሸጥ እና ሌሎች ወንጀሎችን ለማስቀረት ይጠቅማል፡፡

በአጠቃላይ፤ በሀገራችን እየተገነቡ ላሉት እና ለሚገነቡት ፕሮጀክቶች የራስን አሻራ በተለያዩ መልኮ ማኖር ከማስታወሻነቱ እና ከመታሠቢያነቱ ጋር ስምን ማስነሳት እንደሚሆን ከዓድዋው መታሰቢያ ሙዚየም እንድንማር እናሳስባለን፡፡

ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ አካሉ ጴጥሮስ ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
ሰሎሞን ወርቁ

ጰሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 11-6-17-84-90 ኮድ 8490 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት፡- www.mor.gov.et ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia

ስታክስ እና ስጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ፡- 8199

በስኬት የታጀበው ...

ከገጽ 1 የዞረ

በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደረጃ የሞያሌ፣ የአዋሽ፣ የመቀሌ፣ የቦሌ ኤርፖርት እና የቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የመርታት አቅም 92 በመቶ ሆኗል፡፡

በገቢዎች ሚኒስቴር በኩል ባለፉት ሰባት ወራት ከሃገር ውስጥ ገቢ እና ከወጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ 312 ቢሊየን 148 ሚሊየን 500ሺ 293 ብር ለማግኘት ታቅዶ 302 ቢሊየን 419 ሚሊየን 536ሺ 394 ብር ተገኝቷል፡፡ በዚህም የዕቅዱን 96.88 በመቶ ማሳካት ተችሏል፡፡ ይህም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ16.79 በመቶ ብልጫ አለው፡፡ ይሁን እንጂ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከሚያመነጨው አንጻር እየተሰበሰበ ያለው ታክስ እና ቀረጥ በቂ እንዳልሆነም በግምገማው ተገልጿል፡፡

በዚሁ የአፈጻጸም ጊዜ 5ሺ 638 ግብር ከፋዮችን ወደ ታክስ መረቡ ለማስገባት ታቅዶ 6ሺ 905 ግብር ከፋዮችን በማስገባት የዕቅዱ 122.47 በመቶ ተሳክቷል፡፡

የኢንተርኔት መቆራረጥ፣ አንዳንድ የማምረቻ ድርጅቶች ደረሰኝ ያለመቁረጥ፣ የኦዲት አዝማሚያውን በማየት የአንዳንድ የንግድ ድርጅት ባለቤቶች መሰወር እና አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ለታክስ ያበረከተው አስተዋጽኦ አነስተኛ መሆን ዘላቂ መፍትሄ እንዲኖራቸው በትኩረት ሊሠራባቸው እንደሚገባ ከተሰብሳቢዎች አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡

በማጠቃላይው፤ ለገቢ አሰባሰብ አቅም ሊሆኑ የሚችሉ የገቢ ምንጮች ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ፣ የየዘርፎቹ አመራሮች በሳል የአመራር ዘይቤን መከተል እንዳለባቸው፣ ወጥ የሆነ የአሠራር ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ እና ለሁሉም ተገልጋይ ሚዛናዊ የሆነ አገልግሎት በመስጠት ጠንካራ ተቋማትን መፍጠር እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፡፡

የማር እና ...

ከገጽ 5 የዞረ

የተስተካከለ የአተነፋፈስ ስርዓት እንዲኖር ያስችላል፡፡

የጠራ ቆዳ እንዲኖር፡- እኩል መጠን ሎሚ እና ማር በመደባለቅ ቆዳችን ላይ ጠቆር ያለ ምልክት ባለበት ቦታ ላይ በመቀባት ከ20 እስከ 30 ደቂቃ አቆይቶ በቀዝቃዛ ውሃ መታጠብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ማር እና ሎሚን መጠቀም ቆዳችንን ከድርቀት እና ከኢንፌክሽን ይከላከላል፡፡

ከጉንፋን ስመፈወስ፡- ማር እና ሎሚ በውስጣቸው ቪታሚን ሲ ስላላቸው ጉንፋን አምጪ ባክቴሪያዎችን የመከላከል አቅም አላቸው፡፡ ግማሽ ሊትር ውሃ፣ ሦስት የሻይ ማንኪያ ማር እና ሦስት የሻይ ማንኪያ ሎሚ እንዲሁም ዝንጅብል ጨምሮ አንድ ላይ በማፍላት መጠጣት ከጉንፋን ይከላከላል፡፡

ብጉርን ስማጥፋት፡- ሎሚ እና ማር አንድ ላይ ደባልቆ በመቀባት ቆዳ ላይ ያለ ብጉር ደርቆ እንዲረግፍ ማድረግ ከብጉር የፀዳ ቆዳ እንዲኖር ያስችላል፡፡

ለብ ያለ ውሃ ውስጥ ሎሚ በመጨመር በየቀኑ የመጠጣት ጥቅሞች

1. ለብ ባለ ውሃ ውስጥ የሎሚውን ጭማቂ (ፈሳሽ) ብቻ ሳይሆን የሎሚውን ልጣጭም ከ'ተን መጠጣት ጉበትን ከመርዛማ ነገሮች ያፀዳል፤
2. ጉበት ሐሞት እንዲያመነጭ በማድረግ ቅባታማ ምግቦችን ሰውነት እንዲፈጭ ይረዳል፤
3. ከፍተኛ አንቲ ኦክሲደንት ባህሪ ስላለው ሕዋሳታችን (cells) እንዳይወድሙ ይጠብቃቸዋል፤
4. በሎሚ ውስጥ ያለው አንቲ-ኦክሲደንት እና ፊቶኬሚካልስ የጉበት ሕዋሳት እንዲታደሱ ይረዳል፡፡
5. በሎሚ ውስጥ ያለው ሲትሪክ አሲድ የምግብ ሥርዓተ-ልመትን ያፋጥናል፤ የኩላሊት ጠጠርን (kidney stoneን) ያሟሟል፡፡
6. ሎሚ ከሰውነት ውጭ አሲድ ሲሆን በሰውነታችን ውስጥ አልካላይን ስለሚሆን በሰውነት ውሰጥ ያለውን የፒ ኤች ደረጃ ሚዛናዊ እንዲሆን ይረዳል፤ ከበሽታም ይከላከላል፤
7. በሎሚ ውስጥ ያለው ከፍተኛ መጠን ያለው የቫይታሚን ሲ ንጥረ-ነገር ጠንካራ የተፈጥሮ የበሽታ መከላከል አቅም እንዲኖረን ያስችላል፤
8. ሎሚ የደም ቅባትን በመሰባበር ብዙ ሰዎች የሚያጋጥማቸውን የሀሞት ጠጠር (gall stones) በሰውነታችን ውስጥ እንዳይፈጥር ያግዛል፤
9. ሎሚ ከፍተኛ የቫይታሚን ሲ ንጥረ ነገር ስላላው የዩሪክ አሲድ መጠንን በመቀነስ ሰዎች በሪህ (Gout) እና በአጥንት አንጓ እንዳይጠቁ ያደርጋል፤
10. ሎሚ ከአንዳንድ የካንሰር በሽታዎችም ይከላከላል፡፡

እንግዳችን

አዘጋጅ:- ሺመልስ ሲሳይ

«የዓለም አቀፉ የጉምሩክ ድርጅት አባል በመሆናችን ብዙ ጥቅም አግኝተናል»

- አቶ ፍቃዱ በቀለ (የሚኒስትር የጉምሩክ ዘርፍ አማካሪ)

ዓለም አቀፋዊ ባህሪ ካላቸው የመንግሥት ተቋማት መካከል የጉምሩክ መ/ቤት ተጠቃሽ ነው። ይህንን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ዓለም አቀፉ የጉምሩክ ድርጅት የተመሠረተ ሲሆን ኢትዮጵያም የዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅት አባል ነች። ይህንን እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን አስመልክቶ የገቢዎች ሚኒስትር የጉምሩክ ዘርፍ አማካሪ ከሆኑት ከአቶ ፍቃዱ በቀለ ጋር ቆይታ አድርገናል።

ዓለም አቀፉ የጉምሩክ ድርጅት መቼ ተመሠረተ?

ዓለም አቀፉ የጉምሩክ ድርጅት እ.ኤ.አ በ1952 የተመሰረተ ሲሆን ድርጅቱ ሲመሠረት "የጉምሩክ ትብብር ምክር ቤት" በሚል ስያሜ ነበር። ድርጅቱ የተመሰረተበት ዓላማ የአባላት ሃገራትን የጉምሩክ መሥሪያ ቤቶች ብቃትና ውጤታማነት ለማሳደግ ነው። ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት 183 አባል ሃገራት የጉምሩክ መ/ቤቶች የሚወከሉበት እና 98 በመቶ የሚሆነውን የዓለም ንግድ እንቅስቃሴ የሚያስተናግድ ነው። ኢትዮጵያም ከ1965 ዓ.ም ጀምሮ የዚሁ ድርጅት አባል ነች ።

ድርጅቱ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል?

በዓለም አቀፍ ንግድ እንቅሰቃሴ ውስጥ የንግድ ዕቃዎች ዓለም አቀፍ ድንበር ይሻገራሉ። ይህም እንቅስቃሴ በተገቢው መልኩ መመራት ይኖርበታል። ለዚሁም ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መኖር እና እነዚህ ስምምነቶችም ተግባራዊ መደረግ ይኖርባቸዋል። እነዚህን ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶች ማስተዳደር እና ተግባራዊነታቸውን ማረጋገጥ የድርጅቱ ዋንኛ ተግባር ነው።

ዓለም የጠበቀ ቁርኝት እንዲኖራት ከሚያደርጉ ጉዳዮች ውስጥ ንግድ አንዱ ነው። የንግድ ሥርዓቱ ዓለም አቀፋዊ ይዘቱን ጠብቆ መጓዝ ይኖርበታል። ስለዚህ ዓለም አቀፋዊ ንግዶች ይዘታቸውን ጠብቀው እንዲጓዙ ማድረግ የዚህ ድርጅት ኃላፊነት ነው።

በዓለም አቀፍ ንግድ ደረጃ ወጥ የሆነ አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ የተካሄዱት ስምምነቶች ምን ምን ናቸው?

የዓለም የጉምሩኮች ድርጅት ዘመኑን የዋጀ አገልግሎቶች ለመስጠት በርካታ ስምምነቶች እንዲደረጉ ጥሯል። ስምምነቶቹም፤ "የተሻሻለው የኪዮቶ ስምምነት" ተብሎ የሚታወቀው እና የጉምሩክ የሥራ ሂደትና ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸምን የሚመለከት ዓለም አቀፍ ስምምነት፣ የጉምሩክ ታሪፍ አመዳደብን የሚመለከት የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየም እና አመዳዳብ ሥርዓት ዓለም አቀፍ ስምምነት፣ ከዓለም ንግድ ድርጅት ጋር በመተባበር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚተገበር የዓለም ንግድ ድርጅት የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ስምምነት፣ ከዓለም ንግድ ድርጅት ጋር በመተባበር በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚተገበር የዕቃዎች የሥሪት አገር አወሳሰን ሥርዓት ናቸው።

ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች አንጻር የሃገራችን የጉምሩክ ሕግ ማሻሻያ ምን ይመስላል?

የኢትዮጵያ የጉምሩክ አዋጅ ከዓለም ጉምሩክ ድርጅት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በተደጋጋሚ ጊዜያት ማሻሻያዎች ተደርገዋል።

ሀገራት ዓለም አቀፍ የጉምሩክ ስምምነቶችን በመፈረም እና በፓርላማ በማጸደቅ አሊያም ዓለም አቀፍ ስምምነቶቹ ሳይፈረሙ እና በፓርላማ ሳይጸድቁ በቀጥታ በጉምሩክ አዋጅ ውስጥ ማካተት እንደሚቻል ዓለም አቀፉ ድንጋጌዎች ይፈቅዳሉ።

ኢትዮጵያ ፈርማና በፓርላማ አጸድቃ ተግባራዊ ያደረገቻው ከጉምሩክ ጋር የተያያዘ ዓለም አቀፍ ስምምነት የዓለም ጉምሩክ ድርጅት የሸቀጦች አመዳደብና አሠያየም ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽንን ብቻ ነው። ሌሎቹ በጉምሩክ አዋጅ ውስጥ የተካተቱት የዓለም ጉምሩኮች ደርጅት የተሻሻለው የኪዮቶ ስምምነት እና የዓለም ንግድ ድርጅት የጉምሩክ ዋጋ አተማመን ስምምነት ሳይፈረሙ እና በፓርላማ ሳይጸድቁ በቀጥታ በጉምሩክ አዋጅ ውስጥ የተካተቱ ናቸው።

ሌላው አዋጅ ቁጥር 60/1989 ነው። ይህ የጉምሩክ አዋጅ ለሁለት ዓመታት ካገለገለ በኋላ ከዘመኑ የወጪና ገቢ ንግድ እንቅስቃሴ አፈጻጸም ጋር ጋር አብሮ ስለማይሄድ የጉምሩክ አሠራሩን ይበልጥ ማዘመን አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ሌላ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 እንዲወጣ ተደርጓል። ይህ አዋጅ ከዓለም አቀፍ ንግድ እንቅስቃሴ ጋር የሚጣጣም፣ ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ እና ሀገሪቷ የፈረመቻቸውን ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና አካባቢያዊ የንግድ ስምምነቶች የአሠራር ሥርዓቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ያስገድዳል። በዚሁም ከአዋጅ ቁጥር 60/1989 ጋር ሲነጻጸር በርካታ ጉዳዮችን አሻሽሏል።

አዋጁም በዓለም ንግድ ድርጅት የዋጋ አተማመን ስምምነት ውስጥ የተካተቱትን ስድስቱንም የዋጋ አተማመን ዘዴዎች እና አንድ ዘመናዊ ጉምሩክ አዋጅ ሊያካትተው የሚገባ የድሕረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ድንጋጌዎችን ያካተተ ነበር።

የጉምሩክ አሠራሮችን ይበልጥ ዘመናዊ እና ዓለም አቀፋዊ የጉምሩክ አሠራሮችን ተግባራዊ ለማድረግ በ2007 ዓ.ም ሌላ አዲስ የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ወጥቷል። አዋጁ በዋነኛነት ዓላማ ያደረገው በአገራችን እያደገ የመጣውን የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ልማት የሚደግፍ እንዲሁም ሕጋዊ ንግድና ኢንቨስትመንትን የሚያበረታታ የጉምሩክ አሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋት ነው። በተጨማሪም የጉምሩክ አዋጅ ከዓለም ንግድ ድርጅት ስምምነቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆንና በዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድር ወቅት በአዋጅ ቁጥር 622/2001 ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተዋል ለተባሉ ቃላት እና ሐረጎች ምላሽ የሰጠም ነበር። በተጨማሪም አዋጅ ቁጥር 1160/2011 እንዲወጣ የተደረገ ሲሆን የዚህ አዋጅ ዓላማ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ውስጥ ያልተካተቱ አዳዲስ ድንጋጌዎች እንዲካተቱበት ለማድረግ ነው።

ኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ የጉምሩክ ድርጅት አባል መሆኗ ምን ምን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል?

ከተመሠረተ 72 ዓመታትን ያስቆጠረው ይህ ድርጅት በነዚህ ዓመታትም በርካታ ልምዶችን አካብቷል። ሀገራችን የዚህ ድርጅት አባል መሆኗ በርካታ ጠቀሜታዎችን አስገኝቶላታል። ከነዚህ ጠቀሜታዎች ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን እያደረገች ያለውን ጥረት መደገፍ ነው። ድርድሩ የተጀመረው በ1995 ዓ.ም ሲሆን በተለያዩ ውስጣዊ እና ውጫዊ ችግሮች የተነሳ የድርድሩ ሂደት እንደተጠበቀው ሊሆን አልቻለም። ይህንን ድርድር ለማሳካት የዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅት አባል መሆን የራሱ አወንታዊ ሚና ይኖረዋል።

ሌላው ጠቀሜታ፤ ኢትዮጵያ በርካታ ዓለም አቀፍ የጉምሩክ ስምምነቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች። የነዚህ ስምምነቶች ተግባራዊ መሆን በሃገሪቱ ተወዳዳሪ የሆኑ አገልግሎቶችን ለመስጠት ያግዛል።

ዓለም አቀፋዊ አሠራሮች ተግባራዊ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የድርጅቱ ተቀዳሚ ዓላማ ነው። የእነዚህ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው አሠራሮች ተግባራዊ መሆን አገልግሎቶችን በዘመናዊ መልኩ ለመስጠት የላቀ ሚና አለው።

ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ- ሰለሞን ወርቁ

ስለሂሳብ መዝገብ አያያዝ

በመሰንበት አድማሱ

1. የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ማለት ምን ማለት ነው?
- የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ማለት ለትርፍ ይሁን ትርፍ ለማያስገኝ የንግድ ወይም ንግድ ያልሆኑ ሥራዎችን በመሥራት ሂደት ልንከተለው የሚገባ የመረጃ ሥርዓት ነው፡፡

2. የሂሳብ መዝገብ ለመያዝ የሚያስችሉ ቅድመ-ሁኔታዎች
- ሙያው በሚጠይቀው የትምህርት መስክ በቂ ትምህርትና ልምድ ያለው ባለሙያ፤
- የድርጅቱ ቋሚ ንብረቶች መዝገብ፤
- ገቢ ለመሰብሰብ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተፈቀዱ የገቢ ደረሰኞች (የታተሙ፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ፣ በኮምፒዩተር ሲስተም የተዘጋጁ ወይም በኤሌክትሮኒክስ የሚዘጋጁ)፤
- የወጪ ማረጋገጫ (የገንዘብ መክፈያ ሰነዶች)፤
- በቆጠራ የተረጋገጡ የንግድ ዕቃዎች ዓይነት፣ መጠን እና ዋጋ፤
- የባንክ ሰነዶች እና የባንክ ሂሳብ መግለጫዎች፤
- የንግድ ውሎች፣ የመድን ዋስትና ስምምነቶች፣ ወ.ዘ.ተ፡፡

3. የሂሳብ መዝገብ መያዝ ለታክስ ከፋዩ እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰጠው ጠቀሜታ
- ለታክስ ከፋዩ የሚሰጠው ጠቀሜታ
- የሂሳብ መግለጫዎችን ለማዘጋጀት (የሃብትና ዕዳ፣ የትርፍ ወይም ኪሳራ፣ ወ.ዘተ)፤
- የታክስ ሕግ ተገዥነት ግዴታን ለመወጣት፤
- የታክስ ከፋዩን የሂሳብ ሰነዶች ለፋይናንሻል ኦዲት እና ለታክስ ኦዲት ዝግጁ ለማድረግ፤
- የንግድ እፎይታ ተጠቃሚ ለመሆን እና ኪሳራን ለማሸጋገር፣
- በንግዱ ዙርያ ውሳኔ ለመስጠት፤
- የንግድ እንቅስቃሴን ፋይናንስ ለማድረግ፤
- ከንግድ ጋር ተያያዥ በሆኑ ክርክሮች ላይ በማስረጃነት ለመጠቀም፤
- ሌሎች በሕግ የተደነገጉ የግብር መወሰኛ ዘዴዎችን ለማስቀረት፡፡
- ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚሰጠው ጠቀሜታ፡-
- የታክስ ከፋዩን የታክስ ሕግ ተገዥነት ለማረጋገጥ፤
- ታክስ ከፋዩን ለማስተማር፤
- ታክስ ማጭበርበርን በመከላከል ወይም በመቆጣጠር ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ፤
- የታክስ እና የንግድ ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ፡፡

4. የሂሳብ መዝገብ መያዝ የሚገባቸው ግብር ከፋዮች
- በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ድንጋጌ መሠረት የሂሳብ መዝገብ መያዝ የሚኖርባቸው የደረጃ 'ሀ' እና 'ለ' ግብር ከፋዮች ሲሆኑ በራስ ፈቃደኝነት የሂሳብ መዝገብ እንዲይዙ የሚፈቀድላቸው ደግሞ የደረጃ 'ሐ' ግብር ከፋዮች ናቸው፡፡

5. የሂሳብ መዝገብ መያዝ ሲኖርባቸው ያልያዙ ታክስ ከፋዮች ላይ የሚጣለው ሕጋዊ ቅጣት
- የሂሳብ ሰነዶችን ወይም የሂሳብ መዝገብ መያዝ ሲኖርባቸው ያልያዙ ታክስ ከፋዮች በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 102 መሠረት ሊከፍሉት የሚገባውን ታክስ 20 በመቶ ቅጣት ይከፍላሉ፡፡

6. የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች
- ታክስ ከፋዮች የንግድ ወጪዎችን ለመያዝ ተገቢነት ያላቸውን ሰነዶች ያለማግኘት፤
- በታክስ ሕጎች ላይ በቂ ግንዛቤ ያለመኖር፤
- ታክስ ከፋዮች ለሚኒስቴር መ/ቤቱና ለሌሎች ተቋማት የተለያዩ የሂሳብ መግለጫዎችን የሚያቀርቡ መሆኑ (አልፎ አልፎ የሚያጋጥም)፤
- የሚያቀርቧቸው ዝርዝር የሂሳብ መግለጫዎች ከአጠቃላይ የሂሳብ መዝገቡ ጋር የማይጣጣም መሆኑ፡፡

7. የሂሳብ መዝገብ በየትኛው ባለሙያ ይያዛል?
- የሂሳብ መዝገብ ሊያዝ የሚገባው ከከፍተኛ የትምህርት በአካውቲንግ ወይም ተዛማጅ የትምህርት የተመረቁና በሙያው ተገቢው ዕወቀትና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ናቸው፡፡

8. ታክስ ኦዲት እንዴት ይከናወናል?
- ታክስ ኦዲት የሚከናወነው በታክስ ሕግ ተገዥነት ስጋት መሥፈርቶች መሠረት በተመረጡ ታክስ ከፋዮች የሂሳብ መዛግብት ላይ ነው፡፡
- ታክስ ከፋዮች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ባቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት በአዋጅ ከተደነገጉ የታክስ ሕጎችና ተቀባይነት ባላቸው የሂሳብ መዝገብ አያያዝ መርሆዎች አንፃር ኦዲት የሚደረጉ ሲሆን የኦዲት ከኦዲት የመግቢያ ውይይት እስከ ታክስ ውሳኔ መስጠት ያለው ሂደት ታክስ ከፋዮች እንዲያውቁት የሚደረግበት አሠራርን በመከተል የሚከናወን ነው፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ (ተእታ) /value added tax/

በሕይወት ከበደ

የተጨማሪ እሴት ታክስ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የንግድ ሰዎች በሆኑት በጀርመናዊው ነጋዴ ዊልሄልም ቮን ሲመንስ እና በአሜሪካዊው ቶማስ ኤስ አዳምስ የተዘጋጀ የታክስ አይነት ነው፡፡ ታክሱ ሲጀመር አጠቃላይ የሽያጭ ታክሶችን በመተግበር ላይ የተፈጠሩትን አሳሳቢ ችግሮች ለመፍታት በሚያስችል መንገድ ነበር፡፡

በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ አጋማሽ ላይ በታክስ መዋቅር ለውጥ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ክስተት እንደሆነ በበርካታ የዘርፉ ምሑራን ዘንድ የታመነበት ይህ ታክስ በብዙዎቹ የአውሮፓ ሀገራት እ.ኤ.አ በ1960ዎቹ እና 1970ዎቹ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በ1980ዎቹ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ ሌሎች አገሮች እነሱን በመከተል ሕጎቹን ተግባራዊ ማድረግ ጀመሩ፡፡

በአገራችንም ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 ወጥቷል፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16/1 እና 18/6 መሰረት ብዙዎቹ ተመዝግበው የሚጠበቅባቸውን የታክስ ግዴታ በመወጣት ላይ ይገኛሉ፡፡

ለታክሱ ተመዝጋቢዎች የነበሩት ታክስ የሚከፈልበት ዓመታዊ ግብይታቸው ከ500ሺ በላይ የሆነው የነበረ ሲሆን በኋላ ላይ የገንዘብ መጠኑ ተሻሽሎ ዓመታዊ ግብይታቸው ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ናቸው፡፡

ዓመታዊ ግብይቱ ከአንድ ሚሊየን ብር በታች የሆነ አንድ የንግድ ድርጅት ዕቃ ከሚያቀርብላቸው ድርጅቶች 75 በመቶ እና ከዚያ በላይ የሆኑት የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆኑ በፈቃደኛነት ለታክሱ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

ታክሱ ሽያጭ ሲፈጸም ወይም አገልግሎት ሲሰጥ ከገዢው 15 በመቶ በዕቃው ወይም በአገልግሎቱ ላይ የዋጋውን 15 በመቶ ተጨምሮ የሚሰበሰብ ነው፡፡ ዕቃውን የገዛው ለቀጣይ ሲሸጥ የሽያጩን 15 በመቶ ጨምሮ ካስከፈለ በኋላ እርሱ ሲገዛ የከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አስቀርቶ ከትርፉ ላይ 15 በመቶ ለመንግሥት ገቢ ያደርጋል፡፡

የቤት ኪራይ ገቢ ግብር ተቀናሽ ወጪዎች

የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ

- በአንድ የግብር ዓመት የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሰላበት ጊዜ የሚከተሉት ወጪዎች በተቀናሽ ይያዛሉ፡-

1. ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለመንግሥት ወይም ለከተማ አስተዳደር በግብር ዓመቱ ውስጥ የከፈላቸው ክፍያዎች፤
2. ለቤቶች፣ ለቤት ዕቃ እና መሳሪያ ማደሻ፣ መጠገኛ እና የእርጅና መተኪያ የሚሆን ከቤት ዕቃና ከመሣሪያ ኪራይ ከሚገኘው ጠቅላላ ገንዘብ ላይ 50 በመቶ፤
3. ከላይ የተመለከተው 50 በመቶ ተቀናሽ በማናቸውም ሁኔታ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ላለባቸው ግብር ከፋዮች ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ያለበት ግብር ከፋይ

1. ገቢውን ለማግኘት የወጡ እና በግብር ከፋዩ የተከፈሉ አስፈላጊ የሆኑ (ገቢውን ለማግኘት፣ ዋስትና ለመስጠት እና ሥራውን ለማስቀጠል የወጡ) ወጪዎች ተቀናሽ ይደረጋሉ፤
2. ቤቱ ያረፈበት የመሬት ኪራይ፣ የጥገና ወጪ፣ የእርጅና ቅናሽ፣ ወለድና የመድን አርቦን፣ ታክስን ሳይጨምር ለመሬቱ ወይም ከተከራየው ቤት ጋር በተገናኘ ግብር ከፋዩ ለከተማ አስተዳደር የከፈላቸው ክፍያዎች፤
3. በነፃ ወይም በኪራይ በያዘው ቤት ስም የሚከፈሉ የውሃ፣ የስልክ እና የመብራት ወጪዎች በውል ውስጥ ተከራይ እንዲከፍል ከተገለጸ ወጪው ስለማውጣቱ ደረሰኝ ሲቀርብ ይያዝለታል፤
4. የኪራይ እና የመኖሪያው ቤቱ በአንድ የመብራት፣ የስልክ እና የውሃ ቆጣሪ የሚጠቀሙ ከሆነ ለነዚህ የወጣው ወጪ 75 በመቶ በወጪነት ተቀናሽ ሊያዝ ይችላል፤
5. በብድር ለተገኘ ወለድ ክፍያ በወጪነት የሚያዘው ለኪራይ አገልግሎት የወጣ ወጪ ብቻ ነው፤
6. ለኪራይ የሚያስገነባው ሕንጻ በብድር የተወሰደ ከሆነ የብድር ወለድ ወጪ የሚያዘው፡-

ሀ. ሕንጻው እስኪገነባ ድረስ ያለው የሕንጻው ዋጋ ሆኖ በእርጅና ቅናሽ የሚታሰብ ሲሆን፤

ለ. ሕንጻው ተገንብቶ ከተጠናቀቀ በኋላ በወጪነት የሚፈቀድ ይሆናል፤

7. የኪራይ አገልግሎቱን ለማስተዋወቅ የሚወጣ ወጪ የሚያዘው፡-

ሀ. በተለያየ ዝግጅት ላይ ለሚደረግ የማስታወቅ ሥራ ሲሆን ከጠቅላላው ኪራይ ገቢ ሦስት በመቶ ባልበለጠ፤

ለ. ለመገናኛ ብዙሃን ወይም ለማስታወቂያ ድርጅት ከሆነ በሙሉ ተቀናሽ ይሆናል፤

8. ለኪራይ የተገነባው ሕንፃ ለሌላ ዓላማ እስካልዋለ ድረስ ግብር ከፋዩ ሕንፃውን ለኪራይ አገልግሎት ዝግጁ ያደረገ ከሆነ ሕንፃው ባይከራይም ለኪራይ እንደዋለ ተቆጥሮ እርጅና ቅናሹ እንደ ወጪ ይያዛል፤



በየዓይነቱ

አሳሳቢው የልጆች ከልክ ያለፈ ውፍረት

የሕጻናት እና የልጆች እድገት ክትትል እድሜ፣ ክብደት እና ቁመትን ያማከለ ነው። አንድ ሕፃን ወይም ከዚያ ከፍ ያለ ልጅ ከልክ ያለፈ የሰውነት ክብደት ወይም ውፍረት አለው የሚባለው በእድገት ክትትል መመዘኛ ክብደቱ ከቁመቱ ጋር ያለው ልኬት ከዕድሜው /Body mass index/ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን የሚያሳየው ቁጥር ከፍተኛ ሲሆን ነው።

በሕጻናት ላይ ከልክ ያለፈ የሰውነት ክብደት መታየቱን ይበልጥ አሳሳቢ የሚያደርገው በአዋቂነት ዕድሜያቸውም ይህን ችግር ይዘውት ሊቀጥሉ የሚችል ስለሆነ ነው።

አጋላጭ ምክንያቶች

በዘርፉ ላይ ጥናት የሚያደርጉ ባለሙያዎች እንደሚገልፁት፤ የዘረ-መል ተጋላጭነትና የተለያዩ አካባቢያዊ ምክንያቶች በሕጻናት ላይ ለሚከሰት ከልክ ያለፈ ውፍረት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

የዘረ-መል ተጋላጭነት፤ የወላጆች ከልክ ያለፈ ክብደት ልጆች ተመሳሳይ ሁኔታ እንዲኖራቸውና በአዋቂነት ዕድሜያቸውም በተመሳሳይ ከልክ ያለፈ የሰውነት ክብደት የመያዝ እድላቸውን በእጥፍ የሚጨምር ሁኔታ ነው። ወላጆች ከሁለት አንዳቸው ከልክ ያለፈ የሰውነት ክብደት ሲኖራቸው የልጆች ተመሳሳይ ሁኔታ የመኖር እድላቸው የቀነሰ ቢሆንም በዚህ ሁኔታ በታዳጊነት እድሜያቸው ላይ ከልክ ያለፈ የሰውነት ክብደት ያላቸው ልጆች በአዋቂነታቸው ከልክ ያለፈ የሰውነት ክብደት የመያዝ እድላቸው በጣም ከፍ ያለ ነው።

አካባቢያዊ ምክንያቶች

የአመጋገብ ሁኔታና በቂ የሰውነት እንቅስቃሴ አለመኖርም ሌሎቹ የዚህ ምክንያቶች ናቸው። በአሁኑ ወቅት እንደሚስተዋለው ቀለል ያሉና ፈጣን ምግቦች ያለመመገብ እንዲሁም ከቤት ውጪ መመገብ ለተጋነነ ውፍረት ያጋልጣል። ብዙ እንቅስቃሴ የማይጠይቁ ተግባራት፤ ማለትም ለረጅም ጊዜ ቴሌቭዥን መመልከትም ይህን ያስከትላል። እንዲሁም የቪዲዮ እና የኮምፒውተር ጨዋታዎች አብዛኛውን የልጆችን ጊዜ ስለሚወስዱ አካላዊ እንቅስቃሴ የማድረግ፣ በትምህርት ቤትም ሆነ ከዚያ በኋላ ውጪ የመጫወት እድላቸው እንዲቀንስ ሆኗል።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

የዘረኛ ማርከሻ

ዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ፌዴሬሽን /Fédération Internationale de Football Association - Internatinal associartion football federation- FIFA/፤ «በተደጋጋሚ በእግር ኳስ ሜዳዎች ላይ ደጋፊዎች እያሰሙ ያለውን የዘረኝነት መልዕክት የምታገስበት ገደብ ከልኩ ስላለፈ እርምጃ እወስዳለሁ» ብሏል። በዚህም መሠረት፤ የዘረኝነት ስድብ እንደተሰማ ጨዋታው ተቋርጦ የተሳዳቢዎቹ ቡድን ሦስት ነጥብ ተቀንሶበት ለተሰደበው ተጫዋች ቡድን ሦስት ነጥብ ይሰጣል» ብሏል።

ይህ እርምጃ ፊፋ ከዚህ በፊት የሜዳ ላይ ዘረኝነቱ እየከፋ ሲሔድበት ይወስድ ከነበረው ጨዋታዎች ያለደጋፊ እንዲካሔዱ ወይም የተሳዳቢው ቡድን በገንዘብ እንዲቀጣ ከሚያደርገው አሠራር በተጨማሪ ነው።

ዘረኝነት ክፋቱ እንዲህ ዓይነት እርምጃ እስከማስወሰድ ይደርሳል:: እኛም ሀገር የክለቦች ጨዋታ ላይ ለሚታየው የዘረኝነት ቁርቁስ መድሐኒት ነውና የስፖርት ፌዴሬሽኖቻችን ልምዱን ይውሰዱ።

ሌሎች ሰዎች

* የተወለድነው በሌሎች ሰዎች እርዳታ ነው፤
* ስማችንን የተቀበልነው ሌሎች ሰዎች ባወጡልን መሰረት ነው፤
* የገቢ ምንጫችን የሚመጣው ከሌሎች ሰዎች ነው፤
* ክብር እውቅና የሚሰጡን ሌሎች ሰዎች ናቸው፤
* ስንወለድ ገላችንን ለመጀመሪያ ጊዜ ያተቡን፤ ስንሞትም ለመጨረሻ ጊዜ የሚያጥቡን ሌሎች ሰዎች ናቸው።
* ከዚህ ዓለም ስንሰናበት ቤታችን እና ንብረታችን በሌሎች ሰዎች ይወሰዳሉ፤
* ልጆች ሆነን እጃችንን ይዘው በመደገፍ መራመድ ያስለመዱን እና በመጨረሻም ስናረጅ እጃችንን ይዘው በመደገፍ የሚያራምዱን ሌሎች ሰዎች ናቸው፤
* በመወለዳችን ምክንያት በደስታ የተደገሰው እና የተበላውም፤ ስንሞትም በሀዘን የሚደገሰው እና የቀብር ሥርዓታችን የሚከናወነው በሌሎች ሰዎች ነው።

ስለዚህ፤ ራሳችንን ከምንወደው ባልተናነሰ ለሌሎችም ክብር እንስጥ።

የማር እና የሎሚ ጥቅም

ማር እና ሎሚ በተፈጥሮ የያዙት አንቲ አክሲደንት የሰውነታችንን በሽታ የመካለከል አቅም እንዲጨምር የማድረግ ኃይል እንዳላቸው በተለያዩ ጊዜያቶች የተካሄዱ ጥናቶች ያመለክታሉ። ሁለቱም ውፍረትን ለመቀነስ እና ለውበት ለመጠበቂያነት ያገለግላሉ።

ለብ ባለ አንድ ብርጭቆ ውሃ ውስጥ ግማሽ ሎሚ እና አንድ የሻይ ማንኪያ ማር ጨምሮ ሁሌም ጠዋት መጠጣት ቦርጭን ለማጥፋት እና የሰውነታችንን ክብደት ለመቆጣጠር ይረዳናል።

ሎሚ በውስጡ ባለው አንቲአክሲደንት አማካኝነት የስብ ሴሎች እንዲጠፉ ያደርጋል። ማር ደግሞ በተፈጥሮ ኃይል ሰጪ በመሆኑ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ይረዳል።

የተስተካከለ የአተነፋፈስ ስርዓት እንዲኖር:- ለብ ባለ አንድ ብርጭቆ ውሃ ውስጥ አንድ የሻይ ማንኪያ ማር እና ሁለት የሻይ ማንኪያ ሎሚ ጨምሮ ጠዋት ጠዋት መጠጣት የመተንፈሻ አካላችን እንዲፀዳ በማድረግ

ወደ ገጽ 2 ዞሯል

ኢትዮጵያ

- በአፍሪካ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች፤
- ከሌሎች በተለየ አስራ ሦስት ወራት ያላት፤
- ከ80 በላይ ቋንቋ የሚነገርባት፤
- የቡና ተክል ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘባት፤
- 13 ቅርሶችን በUNESCO በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚ የሆነች፤
- የአፍሪካ ትልቁ የገበያ ማእከል የሆነው መርካቶ የሚገኝባት፤
- ከአፍሪካ ናይጄሪያን በመከተል በህዝብ ብዛት ሁለተኛውን ስፍራ የያዘች፤
- የባህር ወደብ ከሌላቸው የዓለም ሀገራት በህዝብ ብዛት ቀዳሚ የሆነች፤
- በአፍሪካ የራሷ ፊደልና ቁጥር ያላት፤
- በዓለማችን ረጅም ርቀት የሚጓዘው የዓባይ ወንዝ መነሻ የሆነች፤
- የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ የሆነች፤
- ከ200 በላይ የቋንቋ ዘዬ የሚነገርባት፤
- ስሟ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቅዱስ ቁርዓን ብዙ ቦታ የተጠቀሰባት፤
- በአፍሪካ የመጀመሪያው የኦሎምፒክ ወርቅ ሜዳልያ ያገኘው አበበ በቂላ መገኛ የሆነች፤
- የተለየ የሰዓት እና የቀን አቆጣጠር ያላት፤
- በአፍሪካ የመጀመሪያው የሆነው መስጊድ መገኛ የሆነች፤
- በቀንድ ከብት ብዛት ከአፍሪካ ሀገራት ቀዳሚ የሆነች፤
- ከ924 የአእዋፍ ዝርያዎቿ በሌላ ዓለማት የሌሉ 23 ወፎች መገኛ የሆነች ሀገር ናት።
- ምንጭ:- ኢንተርኔት

የነፍስ ወከፍ እድሜ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ባለፈው ዓመት የነበረውን የዓለምን የነፍስ ወከፍ እድሜ እንደቀነሰ አንድ ዓለም አቀፍ ጥናት አመልክቷል።

በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የህብረተሰብ ጤና ፕሮፌሰር ናዙር ኢስላም የሚመራው የአጥኚዎች ቡድን ጥናት ያተኮረው በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ እና መከላከኛ ገቢ ባላቸው 37 አገሮች እ.ኤ.አ. ከ2005 እስከ 2019 የሞቱት ሰዎች የነፍስ ወከፍ እድሜ ላይ ነው።

ቢኤምጄ በተባለው የሳይንስ መጽሔት ላይ የወጣው ዘገባ፤ የነፍስ ወከፍ እድሜ በከፍተኛ ደረጃ የወደቀው በሩሲያ መሆኑን ገልጾ የወንዶች በ2.33፤ የሴቶች ደግሞ በ1.14 ዓመት መሆኑን አመልክቷል። ዩናይትድስቴትስ ደግሞ በወንዶች 2.27 እና በሴቶች 1.61 ዓመት በመቀነስ ሁለተኛ ሆናለች።

ጥናቱ ካተኮረባቸው ሀገራት በ31ዱ የነፍስ ወከፍ እድሜ የቀነሰ ሲሆን ቀንሶ ያልታየባቸው ዴንማርክ፣ አይስላንድ፣ ኒውዚላንድ፣ ኖርዌይ፣ ደቡብ ኮሪያ እና ታይዋን ናቸው።

ይህን እና ሌላም ተጽዕኖ ያሳደረው ኮቪድ 19፤ በመላው ዓለም ከአምስት ሚሊዮን በላይ ሰዎችን ሕይወት አሳጥቷል።

ምንጭ:- የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ

ሕግን አለማወቅ...

ከገጽ 8 የዞረ

ወንጀሉን እንደፈፀመ ይቆጠራል" የሚለውን እና የአዋጁን ቁጥር 120/1 "ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከ25ሺ እስከ 50ሺ ብር መቀጫ እና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ይቀጣል" የሚለውን በመተላለፍ ተከሷል። እንዲሁም ሥራ አስኪያጅ ሆነው ድርጅቱን ሲመሩ ድርጅቱ ወንጀል ሲፈጽም ሕጉ የጣለባቸውን የመከላከል ግዴታ ባለመወጣት በፈጸሙት ወንጀል ተከሰዋል።

በሦስተኛ ተከሳሽነት አቶ ዘውዱ ካሰው (የሽየጭ ሠራተኛ/አስተናጋጅ) ሆኖ እያለ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 128 "አንድ ሰው በታክስ ሕግ መሠረት የተደነገገን የታክስ ወንጀል "ዋና ወንጀል" አድራጊ ተብሎ የሚታወቅ ሌላ ሰው እንዲፈጽም የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያገዘ፣ ያነሳሳ ወይም የተመሳጠረ እንደሆነ በዋናው ወንጀል አድራጊ ላይ የተጣለውን ቅጣት ይቀጣል፡፡" የሚለውን እና በአዋጁ ቁጥር 120/1 "ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከ25ሺ እስከ 50ሺ ብር መቀጫ እና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል" የሚለውን ሕግ በመተላለፍ ተጠይቋል። እንዲሁም በአራተኛ ተከሳሽነት የቀረበችውን እና ገንዘብ ተቀባይ የሆነችውን ወ/ሪት ህሊና እዮብን በፈጸመችው የሕግ ጥሰት በመርዳት ወይም በማበረታታት በተመሳሳይ ወንጀል ተከሷል።

የወንጀል ቅጣት ዓላማ ወንጀል አድራጊዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እነዲቆጠቡ እና እንዲታረሙ ማድረግ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ወንጀል አድረገው ከሚቀጡት ሰዎች እንዲማሩ እና ወንጀል ከመፈጸም እንዲጠነቀቁ ማስተማር እንደሆነ የ1996 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1 ላይ ተደንግጓል።

አንደኛ ተከሳሽ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በመሆኑ በወንጀል ሕግ ቁጥር 90/3 መሰረት የሚቀጣው በገንዘብ ነው። ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በገንዘብ የሚያስቀጣ ቢሆንም የእስራት ቅጣቱ ወደ ገንዘብ ሲቀየር እስከ 20ሺ ብር የሚያስቀጣ ነው። በመሆኑም የገንዘብ መቀጫው 25ሺ ብር እና ወደ ገንዘብ ተቀየረው የእስራት ቅጣት 5ሺ ብር በድምሩ 30ሺ ብር እንዲከፍል ተወስኖበታል።

የሁለተኛ ተከሳሽ ሦስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሆን ተወስኖ ይህ ወደ ገንዘብ እንዲቀየር በማድረግ 25ሺ ብር እንዲሁም ተጨማሪ 20ሺ ብር፤ በድምሩ 45ሺ ብር እንዲሆን እና በተከሰሰበት ተጨማሪ ክስ ሁለት ዓመት ከሦስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል።

ሦስተኛው ተከሳሽ ዕድሜው 18 ዓመት ቢሆንም ጥፋቱ በቀላል ደረጃ የሚወሰድ በመሆኑ እና ለዚህም የሚወሰደው እርከን አንድ ከሦስት ዓመት እስከ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ያስቀጣዋል። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ በዚህ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣቱ ሦስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሆን ወስኗል። ይህ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ የ25ሺ ብር እንዲሁም ተጨማሪ 20ሺ ብር፤ በድምሩ 45ሺ ብር ቅጣት እንዲከፍል ወስኖበታል።

አራተኛዋ ተከሳሽ ደግሞ ሁለት ዓመት ከሦስት ወር ጽኑ እስራት እንድትቀጣ ወስኗል። ገንዘብ ተቀባይዋ የ26 ዓመት ወጣት እና በድርጅቱ ከተቀጠረች ገና አንድ ወሯ ቢሆንም ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት አላዳናትምና ከፍርዱ አላመለጠችም።

International...

Continued from page 7

6 / In this Article, "foreign loss", in relation to a resident taxpayer for a tax year, means the amount by which the deductible expenditures incurred by the taxpayer in deriving foreign income taxable under this Schedule exceeds the amount of that income for the year.

Article 48:- Regarding tax treaties

1/ The Minister may enter into a tax treaty with a foreign government or governments.

2/ If there is any conflict between the terms of a tax treaty having legal effect in Ethiopia and this Proclamation,

3/ Subject to sub-article (4) of this Article, when a tax treaty provides that Ethiopian source income is exempt or excluded from tax, or the application of the tax treaty results in a reduction in the rate of Ethiopian tax, the benefit of that exemption, exclusion, or reduction is not available to a body that, for the purposes of the tax treaty, is a resident of the other contracting state when fifty percent or more of the underlying ownership or control of that body is held by an individual or individuals who are not residents of that other contracting state for the purposes of the tax treaty.

4/ If the resident of the other contracting state is: a) a company listed on a stock exchange in that other contracting state; or b) a company carrying on an active business in that other contracting state and the Ethiopian-source income derived by the company is attributable to that business;

5/ In this Article:

a) "Active business" does not include the business of holding or managing shares, securities, or other investments unless the company is a financial institution or insurance company; and

b) "Tax treaty" means an international agreement for the avoidance of double taxation and the prevention of fiscal evasion.

«ሁሉንም ክፍያዎች በባንክ ...

ከገጽ 1 የዞረ

ሚኒስቴሩ ከዚህ በፊት በተፈራረማቸው 19 ባንኮች እና በቴሌ ብር አማካኝነት እስከ ጥር 30/2016 ዓ.ም ድረስ ካሉት ግብር ከፋዮች 45ሺ 212 ወይም 93 በመቶዎቹ በኤሌክትሮኒክ የታክስ አከፋፈል ሥርዓት አሳውቀዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ደግሞ 28ሺ 890 ወይም 53 በመቶዎቹ 182 ቢሊየን ብር ክፍ ፈጽመዋል፡፡

ተ.ቁ	ስምምነት የተፈራረመው ተቋማት	ስምምነት የተካሔደበት እለት
1	ንግድ ባንክ	ሰኔ 2013 ዓ.ም.
2	ዳሽን ባንክ	ሰኔ 2013 ዓ.ም.
3	አዋሽ ባንክ	ሰኔ 2013 ዓ.ም.
4	ብርሐን ባንክ	ሰኔ 2013 ዓ.ም.
5	አቢሲኒያ ባንክ	ጳጉሜን 2013 ዓ.ም.
6	ሕብረት ባንክ	ጳጉሜን 2013 ዓ.ም.
7	ኦሮሚያ ባንክ	ግንቦት 2014 ዓ.ም.
8	ወጋገን ባንክ	ግንቦት 2014 ዓ.ም.
9	ዘመን ባንክ	ግንቦት 2014 ዓ.ም.
10	ቡና ኢንተርናሽናል ባንክ	ሐምሌ 3/2014 ዓ.ም.
11	ደቡብ ግሎባል ባንክ	ሐምሌ 3/2014 ዓ.ም.
12	እናት ባንክ	ሐምሌ 3/2014 ዓ.ም.
13	አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ	ጳጉሜን 1/2014 ዓ.ም.
14	ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ	ጳጉሜን 1/2014 ዓ.ም.
15	ዓባይ ባንክ	ጳጉሜን 1/2014 ዓ.ም.
16	አዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ	ጥቅምት 8/2015 ዓ.ም.
17	ኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ	ጥቅምት 8/2015 ዓ.ም.
18	ሒጅራ ባንክ	ጥር 15/2015 ዓ.ም.
19	ዘምዘም ባንክ	ጥር 15/2015 ዓ.ም.
20	አማራ ባንክ	የካቲት 19/2016 ዓ.ም.
21	ፀሐይ ባንክ	የካቲት 19/2016 ዓ.ም.
22	ኢትዮ ቴሌኮም	ጥር 15/2015 ዓ.ም.

መንገደኞች ያስቀረጥ እና ...

ከገጽ 8 የዞረ

ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ ወይም ከኢትዮጵያ የሚወጣ ሰው ነው፡፡ ነገር ግን በመጓጓዣው ላይ መደበኛ ሥራቸውን እየሠሩ ያሉ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሠራተኞችን እና ተመላላሽ ነጋዴዎችን እንደማይጨምር ደንግጓል።

በዚህም መሰረት ማንኛውም መንገደኛ ቀረጥ እና ታክስ ሳይከፍል ለግል መገልገያ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ዓይነት ዕቃዎች ነው።

- ለስላሳ ሽቶ፡- 500 ሚሊ ሊትር፤
- ሽቶ፡- 500 ሚሊ ሊትር፤
- ሲጋራ፡- 200 ግራም፤
- ሲጋራ፡- በቁጥር 20፤
- ብትን ትንባሆ፡- 250 ግራም፤
- የአልኮል መጠጥ፡- 2 ሊትር፤
- ሞባይል ስልክ፡- በቁጥር 2፤
- ላፕቶፕ፡- በቁጥር 1፤
- የፎቶግራፍ ካሜራ፡- በቁጥር 1፤
- ዊልቸር፡- በቁጥር 1፤
- የእጅ ሰዓት፡- በቁጥር 1፤ Y
- የጺም ወይም የጸጉር መላጫ፡- በቁጥር 1፤
- የጸጉር ማድረቂያ፡- በቁጥር 1፤
- የጸጉር መተኮሻ፡- በቁጥር 1፤
- መንገደኛው የሚጠቀምባቸው መድሐኒቶች እና የህክምና መገልገያዎች፡- በቁጥር (ለአንድ ሰው በሚያስፈልግ መጠን)፤
- በጉዞ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ለቤተሰብ የሚያገለግሉ ልብሶች፣ ጫማዎች እና የጽዳት ዕቀዎች፡- በቁጥር (ለአንድ ቤተሰብ ከሚያስፈልገው ያልበለጠ) ናቸው።

ማንኛውም የግል መገልገያ በስጦታ የተላከለት ሰው፡ - የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሌለው ከሆነ ዕቃው ወደ አገር በሚገባበት ወቅት ሊከፈል ከሚገባው የጉምሩክ ቀረጥ እና ታክስ በተጨማሪ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ላይ የሚሰላ 30 በመቶ የገቢ ግብር እንደሚከፍል ተቀምጧል።

በስጦታ የሚላክለት ዕቃ ዋጋ የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ መሰረት ከሆነው እስከ ማስጫኛ ወደብ ድረስ ካለው ዋጋ (ኤፍ.ኦ.ቢ) ከ1000 የአሜሪካን ዶላር ሊበልጥ እንደማይችል ተቀምጧል። ነገር ግን አንድ ሰው በአንድ ዓመት ውስጥ ከሁለት ጊዜ በላይ ስጦታ ሊቀበል አይችልም። ማንኛውም መንገደኛ በዚህ መመሪያ ከተፈቀደው ውጪ የንግድ ዕቀዎችን ወደ አገር ማስገባት አይችልም።

ምግብ እና ምግብ ነክ የሆኑ፣ መድሐኒቶች እንዲሁም የኮሙኒኬሽን እቃዎችን ይዞ የሚገባ ተመላላሽ መንገደኛ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች የማሳለፍያ ፈቃድ ይዞ መቅረብ አለበት። ይህንንም የሚያደርጉ ባለሙያዎች በአዲስ አበባ ኤርፖርት የመንገደኞች ተርሚናል ውስጥ እንደሚገኙ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ የመንገደኞች ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ካሰች ገ/ዮሐንስ አመልክተዋል።

በዚህ መመሪያ ከተዘረዘሩት እቃዎች ውጪ ለንግድ አገልግሎት የሚውሉ እቃዎችን እንዲሁም በዓመት ሁለት ጊዜ ያልተፈቀደውን እቃ በመንገደኞች መመላለሻ በኩል ይዞ መግባት የተከለከለ ከመሆኑም በተጨማሪ በወንጀል ያስጠይቃል። አንድ መንገደኛ ለግል አገልግሎት ከሚጠቀምባቸው ዕቃዎች ውጪ (ለምሳሌ አንድ ቴሌቪዥን ብቻ ይዞ በመንገደኞች በኩል ቢገባ) መደበኛውን ቀረጥ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ሁለት ይዞ ቢገባ ደግሞ የቀረጥ ክፍያውን ሦስት እጥፍ እንዲከፍል ይገደዳል፡፡ ከዚያ ባለፈ ይዞ ቢገኝ ዕቃው ከመወረሱም በተጨማሪ በወንጀል ይጠየቃል።

አሳሳቢው የልጆች ...

ከገጽ 5 የዞረ

በቀን ውስጥ ለአንድ ወይም ለሁለት ሰዓታት ቴሌቪዥን፣ ኮምፒውተር ወይም ሌላ ትስስር ገፅ ላይ የሚያጠፋ ልጅ በተመሳሳይ ዕድሜ ላይ ከሚገኝ በቂ አካላዊ እንቅስቃሴ ካለው ልጅ ጋር ሲነፃፀር ያነሰ የምግብ አወሳሰድ ቢኖረው እንኳ ከልክ ያለፈ ውፍረት እንዲሁም የደም እና የስብ መጠን መዛባት ይታይበታል፡፡

ሕጻናት በአብዛኛው አመጋገብን እና የምግብ ምርጫዎችን የሚማሩት ከቤተሰብ ነው፡፡ ስለዚህ የልጅን የአመጋገብ ዘይቤ ለብቻ ጤናማ ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ በቤተሰብ ደረጃ ጤናማ አመጋገብን ማዳበር የበለጠ ውጤታማ ያደርጋል፡፡

ከመጠን ያስፈ ውፍረት በልጆች ላይ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

- በጤናማ መንገድ ያልተከተለ የሰውነት ዕድገት፤
- የደም ቅባቶች መጠን መዛባት፤
- የደም ግፊት፤
- የስኳር ሕመም
- የመተንፈሻ አካላት ጤና መታወክ
- የአዕምሮ መቃወስ፤
- ስሜታዊነት
- ከማህበረሰብ መገለል እና ለመግባባት መቸገር
- የጭንቀት ስሜቶች እና
- ሌሎች የጤና እክሎች

ከመጠን ያስፈን ውፍረት መከላከያዎች

- የአመጋገብ ዘይቤን ማስተካከል፤
- አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ፤
- የሥነ-ልቦና ድጋፍ መስጠት፤
- የባሕርይ ለውጥ ሲታይ ባለሙያ ማማከር እና
- ሌሎችም፡፡

ኬብሮን ሠናይ (የሥነ-ምግብ ህክምና ባለሙያ) «ጤናማ አመጋገብ ለጤናማ ቤተሰብ» ከተሰኘው መጽሐፍን ጠቅሶ ከጻፈው የተወሰደ

Tips

BY SHIMELIS SISAY

International tax



The following articles are selected from proclamation No.979/2016 for the purpose of delivering information to the foreign readers.

Article 45:- Regarding foreign tax credit for foreign business income

1/ If a resident taxpayer has foreign income taxable under "Schedule C" in respect of which the resident has paid foreign income tax, the taxpayer shall be allowed a tax credit (referred to as a "foreign tax credit") of an amount equal to the lesser of:

a) The foreign income tax paid: or

b) The business income tax payable under schedule 'C' in respect of the foreign income.

2/ The business income tax referred to in sub-article (1) (b) of this Article shall be computed by applying the average rate of business income tax applicable to the resident taxpayer for the year against the net foreign income of the resident for the year.

3/ A foreign tax credit shall be allowed under this Article only if:

a) the resident taxpayer has paid the foreign income tax within 2 years after the end of the tax year in which the foreign income was derived by the taxpayer or within such further time as the Authority allows; and

b) b) the resident taxpayer has a receipt for the tax from the foreign tax authority.

4./ In computing the business income tax payable by a resident taxpayer for a tax year, the taxpayer shall apply the foreign tax credit under this Article before applying any other tax credits of the taxpayer for the tax year.

5/ If a foreign tax credit of a resident taxpayer for a tax year is not fully credited for the year, the excess credit shall not be refunded, carried back to the preceding tax year, or carried forward to the following tax year.

6/ In this Article:

a) "average rate of business income tax", in relation to a

resident taxpayer for a tax year, means the percentage that the business income tax payable by the tax payer for the year, before the allowance of any tax credit under this Proclamation, is of the taxable income of the taxpayer for the year;

b) "Foreign income tax" means income tax, including withholding tax, imposed by the government of a foreign country or a political subdivision of a government of a foreign country, but does not include a penalty, additional tax, or interest payable in respect of such tax; and

c) "Net foreign income", in relation to a resident taxpayer for a tax year, means the total foreign income of the taxpayer for the year taxable under this Schedule, as reduced by any deductions allowed to the person under this Schedule for the year that:

(1) relate exclusively to the derivation of the foreign income; and

(2) are apportioned to the derivation of the foreign income in accordance with Article 76 of this Proclamation on the basis that foreign income is a separate class of income.

Article 46:- Regarding foreign business losses

1/ An amount that a resident taxpayer is allowed as a deduction under this Proclamation in deriving foreign income taxable under "Schedule C" shall be deductible only against that income.

2/ If a resident taxpayer has a foreign loss for a tax year, the amount of the loss shall be carried forward to the next following tax year and allowed as a deduction in that year against the taxpayer's foreign income taxable under "Schedule C" for the following year.

3/ If a resident taxpayer is not able to wholly deduct a foreign loss under sub-article (2) of this Article, the amount not deducted shall be carried forward to the next following tax year and applied as specified in sub-article (2) of this Article in that year, and so on until the loss is fully deducted, but a taxpayer shall not carry a foreign loss forward for more than five tax years after the end of year in which the loss was incurred.

4. / If there has been two tax years in which a taxpayer has incurred a foreign loss and each of those losses has been carried forward under sub-article (2) of this Article, the taxpayer shall not be permitted to carry forward any further losses under sub-article (2) of this Article.

5/ A taxpayer shall carry forward a foreign loss under sub- articles (2) and (3) of this Article in accordance with the Council of Ministers Regulations.

Continued on page 6

The rights of taxpayers

Any taxpayers have the following rights.

- The right to request information about the Ministry's services or tax rules over the phone or in person.
- The right to get the relevant service without discrimination of gender, race, language, religion, and economic status.
- The right to be treated with respected dignity
- the right to follow up on their issue if they are not responded to immediately. (except for cases that should be kept confidential until the case is completed)
- The Right to express their complaints on the service of the ministry, the discipline of the CEO, and the employees.
- The right to express what they have observed in the ministry and what should be improved or perpetuated in the organization.
- The right to receive awards if they are model taxpayers.

Obligations of the Employers regarding the cost-sharing

- Has to notice the list of employees to the Ministry or other representative body.
- Has to pay 10% of the employee's salary to the Ministry or other representative at the end of 30 months.
- Informing the list of employees who completed the payment and the service to the ministry and other representatives.
- Has to notify the ministry, education minister, and the assigned ministry when they are liable for paying the cost-sharing in service in the case of termination.

Continued on page 6

ሕገ-ግብር

አዘጋጅ:- ሰሎሞን ወርቁ

መንገደኞች ያስቀረጥ እና በቀረጥ ይዘዋቸው ስለሚገቡ ዕቃዎች

ኢትዮጵያውያን ወይም የሌሎች አገራት ዜጎች ለሥራ፣ ለጉብኝት፣ ቤተሰብን ለመጠየቅ ወይም ለሌላ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ሲወጡ ወይም ወደ ኢትዮጵያ ገብተው በሚቆዩበት ጊዜ ተገልግለውባቸው የሚያልቁ ወይም ከተገለገሉባቸው በኋላ ጥለዋቸው ወይም ይዘዋቸው የሚመለሱ የመገልገያ ዕቃዎች አሉ።

ለመገልገያነት የሚውሉትን እነዚህን ዕቃዎች በመለየት መንገደኞች እንዲያውቁት ወደ አገር የሚገቡ ወይም ከአገር የሚወጡ ዕቃዎችን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 923/2014 አለ።

በዚህ መመሪያ መሰረት "የግል መገልገያ ዕቃ" ማለት ጠቅላላ ብዛቱ በዚህ መመሪያ ከተወሰነው መጠን የማይበልጥ፣ ለባለቤቱ ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ ወይም ፍጆታ እንዲውል በዚህ መመሪያ የተፈቀደለት በለሙብት ይዞት ወይም ከባለሙብቱ ተለይቶ ወደ አገር የሚገባ ወይም ከአገር የሚወጣ ዕቃ እንደሆነ በመግለጽ ለንግድ አላማ የማይውል ዕቃ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል።

"ለንግድ የማይውል እቃ" ማለት ደግሞ ጠቅላላ ብዛቱ በዚህ መመሪያ ከተወሰነው መጠን ያልበለጠ ለባለሙብቱ ወይም ለቤተሰቡ የግል መገልገያ ወይም ፍጆታ የሚውል ባለሙብቱ ይዞት ወይም ከባለሙብቱ ተለይቶ የሚመጣ ዕቃ መሆኑን ያስቀምጣል።

በመመሪያው ላይ "መንገደኛ" ማንኛውም በየብስ ወይም በዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያዎች በኩል

... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት አያድንም!

ሁለቱ ሰዎች ወደ ካፌው ገብተው አስተናጋጇን እንዲታዘዛቸው በምልክት ሲጠሩት ቶሎ ደርሶ፣ "ምን ልታዘዝ?" አላቸው። አንደኛዋ ለሁለቱም የሚሆን አንድ ፈጢራ እና ሁለት ሻይ አዝዛ አስተናጋጁ የተባለውን በፍጥነት አመጣላቸው።

ተጠቅመው ከጨረሱ በኋላ ክፍያው ስንት እንደሆነ ሲጠይቁት 170 ብር እንደሆነ ነግሯቸው አንደኛዋ ተስተናጋጅ ድፍን 200 ብር ከፈለች። አስተናጋጁ ደግሞ ለገንዘብ ተቀባይዋ አስተላልፎ 30 ብር ስትመልስለት ከገንዘቡ ሌላ ተጨማሪ የሰጠችው ነገር አልነበረም።

ሁለቱ ሰዎች የተሰጣቸውን መልስ ተቀብለው ከወጡ ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ ግን ከፖሊስ ጋር ተመልሰው መጡ። ፖሊስ ወዲያውኑ የካፊቴሪያውን ሥራ አስኪያጅ፣ ገንዘብ ተቀባይዋን እና አስተናጋጁን በቁጥጥር ስር ካዋላቸው እና ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ ለፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ አሳልፎ ሰጠ።

የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ በአንደኛ ተከሳሽነት "ላ ፋሚሊያ ካፌ እና ሬስቶራንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር"ን በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 120/1 መሰረት "ማንኛውም ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ ያለበት ታክስ ከፋይ ያለደረሰኝ ግብይት ያከናወነ እንደሆነ ከ25ሺ. እስከ 50ሺ. ብር መቀጫ እና ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል" የሚለውን ሕግ መተላለፋቸውን ጠቆመ። ድርጅቱ በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ ከየካቲት 1/2014 ዓ. ም ጀምሮ በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ተመዝግቦ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ተጠቃሚ ነው። ነገር ግን የዓቃቤ ሕግ ምስክር ሆነው ለቀረቡት ሁለት ግለሰቦች በአስተናጋጁ (በሽያጭ ሠራተኛው) አማካኝነት ለተጠቀሙበት

የምግብ አገልግሎት 170 ብር ዋጋ ገንዘብ ተቀባይዋ የአገልግሎት ደረሰኝ መቁረጥ ሲገባት ባለመቁረጧ በተፈጸመ ያለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ ግብይት ማከናወን ወንጀል ክስ መስርቷል።

በሁለተኛ ተከሳሽነት ደግሞ አቶ ሮቤል ከበደ (የድርጅቱን ሥራ አስኪያጅ) የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 132/1 "የታክስ ሕግን በመተላለፍ ወንጀል የፈፀመው ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ በተፈፀመበት ወቅት ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማንኛውም ሰው እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት ይቀጣል" የሚለውን ሕግ በመተላለፍ ተጠይቋል። እንዲሁም በአራተኛ ተከሳሽነት የቀረበችውን እና ገንዘብ ተቀባይ የሆነችውን ወ/ሪት ህሊና እዮብን በፈጸመችው የሕግ ጥሰት በመርዳት ወይም በማበረታታት በተመሳሳይ ወንጀል ተከሷል።

የወንጀል ቅጣት ዓላማ ወንጀል አድራጊዎች ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈጸም እነዲቆጠቡ እና እንዲታረሙ ማድረግ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ወንጀል አድረገው ከሚቀጡት ሰዎች እንዲማሩ እና ወንጀል ከመፈጸም እንዲጠነቀቁ ማስተማር እንደሆነ የ1996 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 1 ላይ ተደንግጓል።

አንደኛ ተከሳሽ የሕግ ሰውነት ያለው ድርጅት በመሆኑ በወንጀል ሕግ ቁጥር 90/3 መሰረት የሚቀጣው በገንዘብ ነው። ጥፋተኛ የተባለበት ድንጋጌ እስከ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እና በገንዘብ የሚያስቀጣ ቢሆንም የእስራት ቅጣቱ ወደ ገንዘብ ሲቀየር እስከ 20ሺ. ብር የሚያስቀጣ ነው። በመሆኑም የገንዘብ መቀጫው 25ሺ. ብር እና ወደ ገንዘብ ተቀየረው የእስራት ቅጣት 5ሺ. ብር በድምሩ 30ሺ. ብር እንዲከፍል ተወስኖበታል።

የሁለተኛ ተከሳሽ ሦስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሆን ተወስኖ ይህ ወደ ገንዘብ እንዲቀየር በማድረግ 25ሺ. ብር እንዲሁም ተጨማሪ 20ሺ. ብር፤ በድምሩ 45ሺ. ብር እንዲሆን እና በተከሰሰበት ተጨማሪ ክስ ሁለት ዓመት ከሦስት ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል።

ሦስተኛው ተከሳሽ ዕድሜው 18 ዓመት ቢሆንም ጥፋቱ በቀላል ደረጃ የሚወሰድ በመሆኑ እና ለዚህም የሚወሰደው እርከን አንድ ከሦስት ዓመት እስከ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ያስቀጣዋል። ስለዚህ ፍርድ ቤቱ በዚህ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ መነሻ ቅጣቱ ሦስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲሆን ወስኗል። ይህ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ የ25ሺ. ብር እንዲሁም ተጨማሪ 20ሺ. ብር፤ በድምሩ 45ሺ. ብር ቅጣት እንዲከፍል ወስኖበታል።

አራተኛዋ ተከሳሽ ደግሞ ሁለት ዓመት ከሦስት ወር ጽኑ እስራት እንድትቀጣ ወስኗል። ገንዘብ ተቀባይዋ የ26 ዓመት ወጣት እና በድርጅቱ ከተቀጠረች ገና አንድ ወሯ ቢሆንም ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት አላዳናትምና ከፍርዱ አላመለጠችም።

የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

እ ሴ ቶ ች

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)